ፓኖራማ ቁጥር 73

# የትዝብት አድማስ

ሐምሌ 1 ቀን 2001 ዓም

## ተተኪውን ትውልድ ማዘጋጀት

ባለፈው ሳምንት ከተለያዩ አካባቢዎች ተወክለው የመጡ የኢትዮጵያ ወጣቶች ጉባዔ አድርገው የኢሕአፓ የወጣት ክንፍ ማኅበር መመስረታቸውን ይፋ አድርገዋል። የኢትዮጵያ ወጣቶች ጉባዔያቸውን በባዕድ ሀገር በማድረግ ድርጅታቸውን ለመመስረት የተገደዱት፥ በአሁኑ ወቅት በሀገራቸው በኢትዮጵያ ውስጥ በነፃነት ለመሰብሰብ ባለመቻላቸው መሆኑ ግልፅ ነው። የኢትዮጵያን ሕዝብ በዘር በመከፋፈል፥ ዴሞክራሲን በማፈንና መሠረታዊ የሆኑትን ሰብዓዊ መብቶች በመግፈፍ፥ የባዕዳንን ጥቅም ለማስጠበቅ ተግቶ የሚሰራው ይህ ዘረኛ ቡድን፥ የኢትዮጵያ ወጣቶች በሀገራቸው ውስጥ እንዳይደራጁ ቢከለክልም፥ ዓላማቸውን ከግብ ለማድረስ የሚያስችላቸውን የኢትዮጵያ ወጣቶች ድርጅትንበባዕድ መሬት ለመመስረት በቅተዋል። ይህ ዜና ለመላው የኢትዮጵያ ወጣቶች ታላቅ የምስራች ሆኗል። የድርጅቱ መሠረት ያው የኢትዮጵያ ወጣቶች ናቸውና የምሥረታው ቦታ የት የት? የሚለው በራሱ ክብድት አይኖረውም። ባበዕድ ሀገር የተመሠረተው ኢሕአፓ የሀገራችን ትልቁ ፓርቲ ሆኖ፥ ስንት ሚሊዮን ሕዝብ አሰልፎ አልነበረምን?

የወጣቶቹ ድርጅት መመሥረት ለኢትዮጵያና ለዜጎቿ የተስፋ ብርሃን ፈንጣቂ ነው። የዛሬው ትውልድ የሚጠበቅበትን ሀገራዊ ኃላፊነት ለመረከብ የሚያስችለውን መሰናዶ እንዲያደርግ የመጀመሪያውን ምዕራፍ ከፍቶለታል ማለት ይቻላል። ቀዳማዊው ትውልድ እያለፈ፥ ተተኪውን ትውልድ ማዘጋጀት አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን፥ ግዴታም ጭምር በመሆኑ የወጣቶቹ መደራጀት የሚጠበቅ ነበር። ከእንግዲህ ወዲህ የሀገርን ጉዳይ አስመልክቶ፥ "የኋላ ልጅ ይጨነቅበት" የሚባል አይደለም። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ችግር ለአንድ ትውልድ ብቻ የሚተውም አይደለም። በሁለንተናዊ ገፅታው፥ ወጣቱን ትውልድ ማዘጋጀት ይዋል-ይደር ተብሎ ለሌላ ጊዜ ሊንከባለል አይገባውም። የኢትዮጵያ ወጣቶች ለሀገራቸው ብሩኅ ተስፋ ለማምጣት በሚያደርጉት ተጋድሎ እንደትላንትናዎቹ ወንድሞቻቸውና እህቶቻቸው ሁሉ በዘርና በሃይማኖት ሳይከፋፈሉ መደራጀታቸው፥ የነገዋን ኢትዮጵያ ትንሳዔ ለማምጣት ዋስትና ነው። እንኳን ደስ ያላችሁ ሊባሉ ይገባል። ከፋፋዮቹም እርማችሁን አውጡ ተብለዋል።

የስድሳ ስድስቱ ዓመተ ምህረት የየካቲት አብዮት የኢትዮጵያ ሕዝብ አንጡራ ገንዘብ ነበር ። ከኢትዮጵያ ሕዝብ ማህፀን ተረግዞ፥ በኢትዮጵያ ሕዝብ የችግር ምጥና የትግል አመፅ ተወልዶ ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ ብሩኅ ተስፋ ለመሆን የመጣ ነበር። ደስታው ወደ ሀዘን፥ ብሔራዊ አንድነቱ ወደ ክፍፍል፥ ተስፋው ወደ ፅልመት፥ የጋራ ዓላማውን ወደ ማጀትና ወደጎጥ፥ አኩሪ ታሪክን ወደ ውርደት፥ ሀገራዊ ዕምነትን ወደ ክኅደት፥ ብልፅግናን ወደ ድኅነት፥ ለመለወጥ አልነበረም። የኢትዮጵያን ብሔራዊ አንድነትና ሉዓላዊነት ሀገራዊ ነፃነትንና የግዛት አንድነትን ድምጥማጥ ለማጥፋት ከቶ አልነበረም። ይህንን ስንል የኢትዮጵያ ጠላቶች፥ "በፈርስ ላይ መጓጎር" ነው እያሉ እንደሚያሾፉ እንገነዘባለን። ይህ ግን የእኛን ቁጭትና ብሔራዊ ዓላማ ሊበርዘው ከቶ አይችልም። ኢትዮጵያን ከወደቀችበት ለማንሳት ወጣቱን ትውልድ ከማዘጋጀት ወደኋላ እንድንል የሚጠበቅ አይሆንም። በዓላማ ፀንቶ ከመታገል የበለጠ ዘለዓለማዊ ሕይወት ሰጭ ስለማይኖር፥ ወጣቱ ትውልድ ለብሔራዊ ዓላማ መደራጀት መቻሉን ማየት ለቀጣዩ ትግል ዋስትና ነው። የኢትዮጵያ ቀጣይ ሕይወትና የወደፊትም ኅልውና ማረጋገጫ ስለሆነ፥ የኢትዮጵያን ጥፋት የመጨረሻውን ምዕራፍ ለማየት ለሚቋምጡት ጠላቶቻችን ተስፋ አስቆራጭ ሆኖባቸዋል። እየተሰው ሀገርን ማዳን ብቻ ሳይሆን፥ ወጣቱን ትውልድ ለብሄራዊ ነፃ አውጭ ትግል ማሰናዳት ማለት፥ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ አሁን ባለችበት ሁኔታ የማትቀጥል ለመሆኗ የሚያረጋግጥ ነው።

በዓለም ታሪክ ውስጥ በተለያዩ ሀገሮች እንደየሀገሮቹ ሁኔታና እንደ ሕዝቦቹ የትግል አካሄድ በርካታ ዓብዮቶች ተካሂደዋል። ዓብዮቱን በመሩት ክፍሎች ችሎታና አያያዝ፥ ሂደትና ውጣ ውረድ አብዛኞዎቹ ግባቸውን ሲመቱ፥ ሌሎቹም ውጤት አልባ ሆነው የቀሩ አሉ። ዓብዮቶቹ የነበረውን ሥርዓት ለመለወጥ ዓላማ ያደረጉ ስለሚሆኑ፥ በሥርዓት ለውጥ አማኞችና ሥርዓቱን አናስለውጥም ባዮች መካከል በግድ ፍጥጫና አመጽ ይፈጠራል። አመጹ ወደ ሞት ሽረት ትግል ይለወጣል። በማህሉ ብዙ ዜጋ ያልቃል። ሀብት ንብረት ይወድማል። የነበረው እንዳልነበር ሲሆን፥ ያልነበረው ወደ መሆን ይሸጋገራል። አብዮቱ እንዲሰምር ከተፈለገ፥ የየሀገሮቹን ሁኔታና ታሪክ የሕዝቦቹንም ባህል፥ ዕምነትና ተስፋ፥ ብሎም የተሻለ የኑሮ ዕድል ለመዘርጋት የሚቻለውን ክስተት ሁሉ አገናዝቦ የሚመራ ኃይል እንዲኖር የግድ ይላል። የዚህ ዓይነት መሪዎች የነበሯቸው አብዮቶች፥ ምንም እንኳ ከተጠበቁና ካልተጠበቁ የሕዝብ ዕልቂትና የንብረት ጥፋት ነፃ ባይሆኑም፤ በተቻለ መጠን ለሀገርና ለሕዝብ የሚጠቅም ውጤት አስመዝግበዋል ።

የኢትዮጵያ የየካቲቱ ዓብዮት ከተከሰተ ከአምስት ዓመት በኋላ የፈነዳው የኢራን ሕዝብ ዓብዮት ያስመዘገው ውጤት ለዚህ አባባል ምሳሌ የሚሆን ነው ለማለት ይቻላል። የታሰበው ዴሞክራሲ ሥርዓት ባይመጣም፥ ኢራኖቹ ሀገራቸውን ከምዕራቡ የእጅ አዙር አገዛዝ ነፃ አውጥተዋል። የሀገራቸውን የነፃነት ልዕልናም ሆነ የሕዝባቸውን አንድነት አላስደፈሩም። በዘመናዊ የዓብዮት ታሪክ እንደ ኢትዮጵያ የየካቲት ዓብዮት ከፍተኛ የሕዝብ ዕልቂት የተማረ ሕዝብ ውድመት፥

ወጣት ፍጅት፥ የሀገርና የሕዝብ ጥፋት ያስከተለ ሀገር የለም ቢባል ማጋነን አይሆንም። ይህ ሁሉ ጥፋት፥ ውድመትና የሕዝብ ዕልቂት ተፈፅሞ ግን ሀገራችን ኢትዮጵያ ወደ ተሻለ ዕድል ተሸጋግራ ቢሆኖ ኖሮ፥ የሀገሪቱ የግዛት አንድነትና ሀገራዊ ሉዓላዊነት ተጠብቆ ቢሆን ኖሮ፥ ወይም ዜጎቿም በዘርና በሃይማኖት እንዲከፋፈሉ ያልተገደዱ ቢሆን ኖሮ፥ የታሪክ ቁጭት ባልነበረም ነበር። የተከፈለውም መሥዋዕት ሁሉ የጠላቶች ሲሳይ ባልሆነም ነበር። ዛሬም የወጣቶችአደረጃጀት ከጎሳ፥ ከሃይማኖትና ከጎጥ አስተሳሰብ የፀዳ ሆኖ፥ እንደ ጥንት-እንደ ጧቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ በአንድ ብሔራዊ ዓላማና ራዕይ መመሥረቱ፥ ወያኔዎቹን ማስደንገጡ የማይጠበቅ አልነበረም። በወጣቶቹ ድርጅትም ውስጥ ሰርስሮ በመግባት ለማፍረስ እንደሚሞክሩም ሳይታለም የተፈታ ነው። ለዚህም ነው የወጣቶቹ ድርጅት በተመሠረተ ማግስት፥ የወያኔ ፕሮፓጋንዳ አገልግሎት የመርበትበትና የመጨነቅ ባኅርይ በተላበሰ መንገድ አፍራሽ ዘመቻውን የቀጠለው። ሦስቱም ተፈራራቂ አምባገነን ሥርዓቶች የወጣቱን ተደራጅቶ መታገል እንደጠር የሚፈሩት ወደው አይደለም። ወጣቱ የለውጥ ፈላጊ ትኩስ ኃይል ነውና! የየካቲቱን አብዮታዊ ሂደት በሚያስደንቅ ፍጥነትና ስፋት ሀገራዊ ይዘቱን በመጠበቅ፥ ሊከሰት ካስቻሉት ዓበይት ምክንያቶች አንዱ፥ የኢትዮጵያ ወጣቶች በብሄር ሳይከፋፈሉ ለአንዲት ኢትዮጵያና ለዜጎቿ የጋራ ጥቅም ተባብረው በመቆማቸውና የጋራ መሥዋዕት በመክፈላቸው ነበር። የአሁኑ ትውልድ ወጣቶችም ይዘውት የተነሱት ዓላማ ዳግማዊ የካቲትን ዕውን ለማድረግ በመሆኑ፥ ለኢትዮጵያ ጠላቶች እንደ አርዕድ-አንቀጥቅጥ ሆኖባቸዋል። የአንድ ሀገር የቀጣይ ኅልውናው ዋስትና፥ ተተኪውን ትውልድ በሁለንተናዊ ገፅታ ማዘጋጀት በመሆኑ፥ ኢሕአፓ ይህንን ተልዕኮ ለማስፈጸምሥራዬ-ጉዳዬ ብሎ ይዞታል። ይህንን የዘረኛ ሥርዓት ለመለወጥ ደግሞ መድኃኒቱ በብሄረሰብ፣ በሃይማኖትና በቋንቋ ልዩነት ያልተበከለ ንፁህ እዕምሮ ያላቸውን የኢትዮጵያ ወጣቶችን አዘጋጅቶ የነፃዋን ኢትዮጵያን እንዲረከቡ ማድረግ ነው።

የነፃዋን ኢትዮጵያ ከክፍፍልና ከክልል በሽታ ለማላቀቅ ዛሬ የሀገሪቱን አድማስ በጤናማ አየር እንዲሞላ ማድረግ ያስፈልጋል። የኢትዮጵያ ህፃናት የሚማሩባቸውን ሥርዓተ-ትምሕርትና የመማሪያ መጻህፍት በሀገር አቀፍ ራዕይና በብሔራዊ ጥቅም ትኩረት ላይ እንዲያነጣጥሩ ማድረግ የዘረኞችንና የከፋፋዮቹን እኩይ ዓላማ ለማክሸፍ ይረዳል። የነገን ብሩኅ ተስፋ ዕውን ለማድረግ ሥራው መሠራት ያለበት ዛሬ ነው። የኢትዮጵያ ጠላቶች ዓላማቸውን ሲጀምሩ፥ ይዘውት የተነሱት መፈክር፥ "ክተት መክት" የሚል እንደነበር ሁሉም የሚያውቀው ነው። ይህ ተተኪው ትውልድ የብሔራዊ ነፃነት ትግል ለመጀመር የሚያስችለውን የራሱን ብሔራዊ የትግል መፈክርና መዝሙር እየዘመረ ጥሪውን ማስተጋባትና እየከተቱ መመከት፥ እየመከቱ ዓላማን/ዒላማን መምታት ይገባል። ለዚህ ሁሉ ደግሞ ወሳኙ በዓላማው የቆመ ቁራጥ አመራር የግድ ይላል። ቁራጥ አመራር ያለው ኢትዮጵያ ወጣት ታምራዊ ተግባራትን እንደሚያስመዘግብ ደግሞ ማንም ሊጠራጠር አይችልም። ይህ ባለፈው ሳምንት ህልውናውን ይፋ ያደረገው የኢትዮጵያ ወጣቶች ድርጅትሀገራዊ ተልዕኮውን ለመወጣት የሚያስችለውን ሁለንተናዊ ትብብር ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደሚለገሰው

ይተማመናል፡፡ የኢትዮጵያን ትንሣዔ የሚመኝ ማንኛውም ዜጋ የነገውን ትውልድ ለመተካት በሚደረገው ብሔራዊ ርብርቦሽ የበኩሉን አስተዋፅዖ የማድረግየዜግነት ግዴታ እንዳለበት ማወቅ ይገባዋል፡፡